M● ST

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# ሀገር አቀፍ የአጠቃላይ ትምህርት የሳይንስና ሒሳብ መምህራን እና ተማሪዎች የሽልማት መመሪያ

**568/2013**

ሚያዝያ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢፌዴሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሀገር አቀፍ የአጠቃላይ ትምህርት የሳይንስና ሒሳብ መምህራን እና ተማሪዎች የሽልማት መመሪያ" ቁጥር **568/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1 "ሽልማት" ማለት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎችና የሚያስተምሩ መምህራን ላስመዘገቡት የላቀ የፈጠራ ስራ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት፣ ሜዳሊያ፤ የገንዘብ እና የስልጠና ማበረታቻ ነው፣

2 "የፈጠራ ስራ" ማለት ተማሪዎችና መምህራን በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የሚሰሩት ናሙና ወይም ሞዴል ነው፣

3 "ጉድኝት ማዕከል" ማለት የተለያዩ ትምህርት ቤቶችን በመረብ የሚያገናኝና የልምድ ልውውጥ የሚያሳዩበት ማዕከል ነው፣

4 "የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት" ማለት ከ5ኛ ክፍል እስከ 8ኛ ክፍል ያለው የትምህርት ደረጃ ነው፣

5 "የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት" ማለት ከ9ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ያለው የአጠቃላይ እና የመሰናዶ የትምህርት ደረጃ ነው፣

6 "አጠቃላይ ትምህርት" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ላይ የተጠቀሱትን የሚያጠቃልል ነው፣

7 "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣

8 "ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ" ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተወዳደሩ ተማሪዎች እና መምህራን የፈጠራ ስራ መረጣን የሚያስፈጽም አካል ነው፡

9 "ኤጀንሲ" ማለት በክልሎች ወይም ከተማ መስተዳድሮች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ነክ ስራዎችን ለመምራትና ለማስተባበር የተቋቋሙ አካላትን ይመለከታል፣

10 በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3 ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ መንግስት ለትምህርት መሻሻል ያስቀመጠውን የትኩረት አቅጣጫ 70/30 ንጽጽርን በመደገፍ ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን ወደ ተግባር በመቀየር የተለያዩ የፈጠራ ስራዎች የሚሰሩ ተማሪዎችን ለማበረታታት፣ በፈጠራ ስራቸው እና በሙያቸው አርአያ የሆኑ የሳይንስ እና የሂሳብ መምህራን እውቅና እና ማበረታቻ መስጠት ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በዘጠኙ ብሔራዊ ክልሎች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ በመንግስት እና የግል የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛ ትምህርት መርሀግብር በሚያስተምሩና የሚማሩ እና የፈጠራ ስራቸውን በሚያቀርቡ ተወዳዳሪ ኢትዮጵያዊያን የሳይንስና የሂሳብ መምህራንና ተማሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የሽልማት ምድቦች፣ ተወዳዳሪዎች ሊሟላት የሚገባቸው
# ቅድመ ሁኔታዎች እና መምረጫ መስፈርቶች

## 5. የሽልማት ምድቦች

በሳይንስ እና ሒሳብ የትምህርት መስኮች የፈጠራ ስራ ለማበረታታት ለመምህራን እና ለተማሪዎች የሚሰጠው ሽልማት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሶስት የሽልማት ምድቦች ይኖሩታል፡፡

1. የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራንና የተማሪዎች ሽልማት ምድብ እና
2. የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሴት ተማሪዎች ሽልማት ምድብ ናቸው፡፡

## 6. ተወዳዳሪዎች ሊሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ መሰረት ለሽልማት የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪዎች፡-

1. በመደበኛ ትምህርት መርሀ-ግብር ሙሉ ጊዜያቸውን በሳይንስና ሂሳብ ትምህርቶች በመምህርነት የሚያገለግሉ ኢትዮጵያውያን መምህራን፣

2. በመደበኛ የትምህርት መርሀ-ግብር የሳይንስ ትምህርት የሚማሩ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል፣
3. በሀገር አቀፍ የሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን በእጩነት የሚቀርቡት ተወዳዳሪ ተማሪዎች እና መምህራን ለክልልና ከተማ መስተዳድሩ በክልሉ ከሚገኙ ብቁ ተወዳዳሪዎች መካከል በዚህ መመሪያ መሰረት በተሰጠው ኮታ ልክ የተሻሉትን በመምረጥ ለሚኒስቴሩ ይላካል፣
4. ተወዳዳሪዎች  በክልል ወይም ከተማ መስተዳድር በሚገኙ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ኃላፊዎች የተፈረመና የተሟላ የማመልከቻ ቅፅ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡
5. ለውድድር የሚቀርቡ የዕጩ ተወዳዳሪዎች የፈጠራ ሞዴሎች እና ናሙናዎች በቡድን የተሰሩ ከሆነ በሚወክሉት አንድ ሰው ስም ለውድድር መቅረብ ይችላሉ፡
6. ለውድድር የሚቀርቡ የግልና የቡድን ስራዎች መረጃ በሰነድ፣ በፎቶ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል ወይም በሌላ አስፈላጊ በሆኑ የማቅረቢያ ዘዴዎች የተደገፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡
7. ከአንድ ትምህርት ቤት የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪዎች በተመሳሳይ ስራ በተናጠል ለውድድር መቅረብ አይችሉም፡
8. ከመምህራንና ተማሪዎች ውጪ የሆኑ የአስተዳደር ስራዎችን ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች በውድድሩ በዕጩነት መቅረብ አይችሉም፡፡

## 7. የመምረጫ መስፈርቶች

1. ለእያንዳንዱ የሽልማት ምድብ የመምረጫ መስፈርቶች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 እና 2 መሰረት ይሆናል፣
2. የእጩ ተወዳዳሪ ተማሪዎችና መምህራን ሥራዎችም የማመልከቻ ቅፁ በሚጠይቀው መሰረት ዝርዝሩን መፃፍ ይኖርባቸዋል፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተወዳዳሪዎች በመምረጫ በመስፈርቱ መሰረት የተሠሩ ሥራዎች በዝርዝር ካልተገለጹ ለመስፈርቱ የተሠጠውን ነጥብ አያገኙም፡፡

# ክፍል ሶስት

## የተሸላሚዎች ድልድልና ብዛት፣ የሽልማቱ አይነት፣ የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት

### 8. የተሸላሚዎች ድልድልና ብዛት

1. ትምህርት ቢሮዎች በየዓመቱ በየሽልማት ምድቡ የሚያቀርቧቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቁጥር በክልልና በከተማ መስተዳድር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችና መምህራን ብዛት አንፃር ሲሆን ዝርዝሩም በሚኒስቴሩ የሚገለጽ ይሆናል፡
2. በአንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ (1) የሽልማት ምድብ ላይ ሴት የሳይንስና ሂሳብ ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ጋር ይወዳደራሉ፡
3. ኤጀንሲው ሴት ተማሪዎችን ለማበረታታት እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተሳትፎአቸውን ለማሳደግ ከወንዶች ጋር ተወዳድረው ያልተመረጡትን ሴት ተማሪዎችን በመስፈርቶቹ መሰረት እርስ በርሳቸው በማወዳደር በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት እንዲካተቱ እጩዎቻቸውን መርጠው ይልካሉ፣
4. በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ለሰፈረው ምድብ በጥቅም ላይ የሚውሉት የመምረጫ መስፈርቶች በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ለተመለከተውም ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

### 9. የሽልማቱ ዓይነት

በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሳይንስና የሂሳብ ትምህርትን ወደ ፈጠራ ውጤት በመቀየር ያሳዩ አሸናፊ ተወዳዳሪ ተማሪዎችና መምህራን፡-

1. የዕውቅና የምስክር ወረቀት፡
2. ሜዳሊያ፡
3. የገንዘብ ማበረታቻዎች የሚያገኙ ሲሆን፡
4. ከተሸላሚ የፈጠራ ሞዴሎች ወይም ናሙናዎች መካከል በመምረጥ በሚዘጋጁ ሀገር አቀፍ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤግዚቢሽኖች ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ ይደረጋል፣
5. ከተሸላሚዎች መካከል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የአጭር ጊዜ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 10. የሽልማት አስተዳደርና የክትትል ስርዓት

1. ሽልማቱን የሚያስተዳድሩትና አፈፃፀሙን የሚከታተሉት ሶስት የፌደራል ሚኒስቴር መስርያ ቤቶች ሲሆኑ እነሱም ሚኒስቴሩ፣ የትምህርት ሚኒስቴርና የሴቶችና የሕፃናት ሚኒስቴር ናቸው፡፡
2. በክልልና የከተማ መስተዳድር ደረጃ ይህንን ሽልማት በበላይነት የሚያስተዳድረው በክልሉ የተቋቋመው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ሲሆን ኤጀንሲው ከትምህርት ቢሮዎች፣ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶችና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ ይሆናል፡፡
3. ከላይ በንዑስ ቁጥር 2 የተገለጸው ቢኖርም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲዎች ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ የሽልማት ጊዜ ብቻ በየክልሉ የሚገኙ የትምህርት ቢሮዎች ይህንን መመሪያ በክልል ደረጃ የማስፈጸም ኃላፊነት ተሰጥቶዋል፡፡
3. የክልልና የከተማ መስተዳድር የትምህርት ቢሮዎች ከክልሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲዎች ጋር በመሆን ከሃገር ዓቀፍ ሽልማት በፊት በመመሪያው መስፈርት መሰረት የየራሳቸውን የፈጠራ መምህራንና ተማሪዎችን አወዳድረው እንዲሸልሙ ሚኒስቴሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

# ክፍል አራት

## የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ

## 11. ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም

በሀገር አቀፍ ደረጃ በተወዳዳሪዎች የተሰሩ የፈጠራ ስራዎች ግምገማና መረጣን የሚያከናውን ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

የኮሚቴው አባላት፡-

1. ሚኒስቴሩ (ሰብሳቢ)
2. ትምህርት ሚኒስቴር (አባል)
3. የሴቶች እና ሕፃናት ሚኒስቴር (አባል)
4. ከሙያው ጋር ተያያዥነት ካላቸው ሊጋር ተቋማትና የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሙያ ማኅበራት ወይም ከህዝብ ክንፍ የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል፡፡

12. የክልልና ከተማ አስተዳደር የግምገማና መሪጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. ከላይ በአንቀጽ 10(2) በተመለከተው መሰረት በክልሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ አስተባባሪነት የሚመራ የሚመለከታቸው አካላትን የያዘ የክልል የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፣ በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት መምሪያዎችና የትምህርት ጽ/ቤቶችም ከእራሳቸው ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ተመሳሳይ ኮሚቴዎች የሚቋቋሙ ይሆናል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት አግባብ ካላቸው አካላት የሚመረጡ ሲሆን የሴቶችና ህፃናት ቢሮ ተወካይ አባል ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት
## ተግባር እና ሀላፊነት

13. የሚኒስቴሩ ተግባር እና ሀላፊነት

1. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ሽልማት በጀት ያስመድባል፣
2. የበጀት ዓመቱን ሽልማት የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ለሚመለከታቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር አካላት ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መርጠው እንዲልኩ ያሳውቃል፣
3. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል መ/ቤቶችን ያስተባብራል፣
4. በየደረጃው የሚካሄደውን የሽልማት አፈጻጸም ክትትል ያደርጋል፣
5. በየሽልማት ምድቡ የሚቀርቡ የተወዳዳሪዎችን መረጃ በማደራጀት የመጀመሪያ መረጣ በማድረግ ለሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ለቀጣይ ግምገማ ዝግጁ ያደርጋል፣
6. የተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፣
7. የላቀ ውጤት ላስመዘገቡት የምርጦች ምርጥ ተሸላሚዎች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፣
8. ውጤታማ የሆኑ ፈጠራዎችንና ምርምሮችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
9. ለተሸላሚዎችም የስራ ፈጠራና የአቅም ግንባታ የአጭር ጊዜ ስልጠና እና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## 14. ሀገር አቀፍ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በሁሉም የሽልማት ምድቦች የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን ሰነድ እና ውጤት ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ፣
2. በተወዳዳሪዎች የቀረቡ የፈጠራና የምርምር ስራዎችን በጥልቀት በማየት በተሰጠው መስፈርት ይገመግማሉ፤ የማለፊያ ነጥብ በማስቀመጥ ለሽልማት ብቁ የሆኑትን በደረጃ ለይተው ያቀርባሉ፣
3. በተወዳዳሪዎች የተሰሩ ስራዎችን በመስፈርቶቹ መሰረት በመገምገም በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤት ይሰጣሉ፣
4. የተመረጡትን እጩ ተሸላሚዎችን ጠቅላላ የአመራረጥ ሂደትና ውጤት ሪፓርት ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃሉ፡፡

## የክልልና ከተማ መስተዳድር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲዎች ተግባር እና ሀላፊነት

1. የሚመለከታቸው አጋርና ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የክልል፤ የዞንና ወረዳ የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ እንዲቋቋም ያደርጋል፣
2. የክልልና ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ለሀገር አቀፍ ሽልማት ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መርጠው ከመላካቸው በፊት በራሳቸው በጀት ብቁ መምህራንና ተማሪዎችን አወዳድረው እንዲሸልሙ ድጋፍ ያደርጋል፣
3. በየሽልማት ምድቡ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እጩ ተሸላሚዎችን ከኮሚቴው ቃለ ጉባኤ እና ከሌሎች ከድጋፍ ሰጪ መረጃዎች ጋር አያይዞ ለሀገር አቀፍ የምርጦች ምርጥ ሽልማት ለሚኒስቴሩ ይልካል፡፡

## የወረዳና የዞን መስተዳድር የሽልማት መራጭ ኮሚቴ ተግባር እና ሀላፊነት

1. የወረዳ ወይም የዞን የሽልማት ኮሚቴ ከትምህርት መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ከሴቶችና ህጻናት መምሪያ እና የሚመለከታቸው አካላት ያካተተ የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
2. እያንዳንዱ ዞን በየሽልማቱ ምድብ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እጩዎችን በመምረጥ ከመራጭ ኮሚቴው ሪፖርት ጋር ደጋፊ መረጃዎችን በማያያዝ ለክልሉ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ይልካል፣

# ክፍል ስድስት

## የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት፣ የቅሬታ አፈታት ስርዓት፣ ክትትልና ግምገማ

### 15. የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት

1. ሁሉም እጩዎች የሚመረጡት በአብዛኛው የሳይንስ ትምህርትን መሰረት በማድረግ በሰሩት የፈጠራ ስራ ሞዴሎች ወይም ናሙናዎች ሲሆን እንደ አግባብነቱ ሌሎች ደጋፊ መመዘኛዎችም ታሳቢ ይደረጋሉ፣
2. የእጩ ተሸላሚ መረጣ የሚጀመረው የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ከሚያስተዳድራቸው ትምህርት ቤቶች ይሆናል፡፡
3. ሁለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ውጤት ካገኙ ተጨማሪ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት እንዲለዩ ይደርጋል፡፡ሆኖም ከሁለቱ ተወዳዳሪዎች አንዷ ሴት ወይም አካል ጉዳተኛ ከሆነች ወይም ከሆነ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡
4. እያንዳንዱ ዞን ወይም ክፍለ ከተማ በሁለቱም የሽልማት ምድቦች ዕጩዎችን በመምረጥ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ስም ዝርዝር እና ደጋፊ መረጃዎችን ፤የጥናት ሰነዶች፣ ፎቶዎችና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ለሚመለከተው የክልል ወይም ለከተማ አስተዳደር ይልካል፣
5. የክልል እና ከተማ መስተዳድር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እጩ ተወዳዳሪዎችን የገምጋሚና መራጭ ኮሚቴውን ቃለጉባኤ፣ ዕጩዎች በየመስፈርቱ የሰሯቸውን ሥራዎችና ማስረጃዎችን በማያያዝ ዝርዝሩን በማጠቃለያ አባሪ ቅጽ ሞልተው ለሀገር አቀፍ የምርጦች ምርጥ ሽልማት ውድድር ለሚኒስቴሩ ይልካሉ፡፡
6. ሚኒስቴሩ ለሀገር አቀፍ ውድድር የቀረቡትን ተወዳዳሪዎች ሰነድና ማስረጃዎችን አግባብነት የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ በማድረግ ለሚቋቋመው ሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ያቀርባል፣
7. የሀገር አቀፍ ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ዕጩ የምርጦች ምርጥ ተሸላሚዎችን በመምረጥ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃል፡፡
8. የፀደቁ የምርምርና የፈጠራ ውጤቶች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ይደረጋሉ፡፡

16. የቅሬታ አፈታት ስርዓት

ተወዳዳሪዎች ወይም ተሸላሚዎች ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሽልማት አመራረጥ ሂደት፣ የተለያዩ አገልግሎቶች እና አሰራሮች ላይ ቅሬታ ካላቸው በሚኒስቴሩ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስነ-ስርዓት መሰረት የሚፈታ ይሆናል፡፡

17. ክትትልና ግምገማ

በየደረጃው ያሉ የሽልማት አስፈፃሚ አካላት የሽልማቱን አፈፃፀም በየጊዜው ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ እንዲሁም የተሸላሚ ተማሪዎችንና መምህራን መረጃ ይይዛሉ፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. የተሻረ መመሪያ

ብሔራዊ የሳይንስና ሂሳብ የፈጠራ ተማሪዎችና መምህራን የሽልማት መመሪያ ቁጥር 7/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

19. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

20. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መጋቢት ..... ቀን 2008 ዓ.ም

አብይ አህመድ

ሚኒስቴር

አብይ አህመድ

ሚኒስትር

አባሪ 1

## ምድብ I. የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችና መምህራን ሽልማት መስፈርትና ክብደት

### ሀ. የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | ክብደቱ ከ100% | መስፈርት | የሚሰጠው ነጥብ መጠን | በግምገማው ያገኘው ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 50% | በትምህርት ቤት አዲስ የተሰሩ የፈጠራ ሥራዎች[1]<br>• የፈጠራ ሐሳብ ማመንጨትና ሐሳብን በራስ ጥረት በተግባር (ሞዴሎች ቻርቶችና ሌሎች) ማሳየት፣ | እስከ 40% | % |
| | | • በትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ውስጥ የተደረገ ተሳትፎ (ሞዴሎች ቻርቶችና ሌሎች፣ የትምህርት መሳሪያዎችን) መስራት | እስከ 5% | % |
| | | • የፈጠራ ሀሳብን ብቻ ማመንጨት እና ጠቀሜታውን መግለፅ | እስከ 5% | % |
| | | | ድምር 50% | ድምር % |
| 2 | 15% | ሽልማቱ በሚሰጥበት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት በሳይንስና በሂሳብ ትምህርቶች ያስመዘገበው አማካኝ የፈተና ውጤት<br>• ከ95 — 100 ያለው | 15% | % |
| | | • ከ90 — 95 ያለው | 13% | |
| | | • ከ85 — 90 ያለው | 11% | |
| | | • ከ80 -- 85 ያለው | 9% | |
| 3 | 15% | በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማር ማስተማር ሒደቱ ውጭ ባሉ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ<br>• ሳይንስን በት/ቤት ሚኒሚዲያ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ፅሑፎች ማዘጋጀት፣ | እስከ 9% | % |
| | | • በት/ቤት የሳይንስ ክበብ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ | እስከ 6% | % |
| | | | ድምር 15% | ድምር % |
| 4 | 15% | በማጠናከሪያ ትምህርቶችና በቡድን ጥናት ለመጠቀምና ክህሎትን ለሌሎች ተማሪዎች ለማካፈል ያለው ተነሳሽነት/ፍላጎት<br>• በማጠናከሪያ ትምህርት ላይ የተደረገ ተሳትፎ፣ | እስከ 5% | % |
| | | • በቡድን ጥናት ላይ የተደረገ ተጨባጭ አስተዋፅኦና አጠቃቀም፣ | እስከ 5% | % |
| | | • ክህሎትን ለሌሎች ተማሪዎች ማካፈልና ማብቃት፣ | እስከ 5% | % |
| | | | ድምር 15% | ድምር % |
| 5 | 5% | የተማሪው ባህሪና ሥነ-ምግባር<br>• ሕግና ደንብን መጠበቅ፣ | እስከ 3% | % |

[1] ያመነጨው አዲስ ሃሳብና በተግባር ያሳዩት የፈጠራ ስራ/ሞዴል፣ ናሙና እና የትምህርት መርጃ መሳሪያ/ ውስብስብነት፣ ብዛት እና ከሳይንስና ሒሳብ ትምህርቶች ያለው ተያያዥነት ከግምት ውስጥ ይገባል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ከደባል ሱስ የፀዳ መሆን | እስከ 2% | % |
| | | | ድምር 5% | ድምር % |
| | | ከ100% ያገኘው ጠቅላላ ድምር ውጤት | | % |

## ለ. የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | ክብደቱ ከ100% | መስፈርት | የሚሰጠው ነጥብ መጠን | በግምገማው ያገኘው ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 45% | በትምህርት ቤት የተሰሩ አዲስ የፈጠራ ስራ ናሙናዎች [2]<br>• ሶስት እና ከሶስት በላይ ናሙናዎች | እስከ 45% | % |
| | | • ሁለት ናሙናዎች | እስከ 40% | |
| | | • አንድ ናሙና | እስከ 35% | |
| 2 | 12% | ከትምህርት ጋር የተጣጣመ ተግባራዊና ውጤት ያለው ምርምርን ማካሄድ[3]<br>• ሶስትና ከዚያ በላይ | እስከ 12% | % |
| | | • ሁለት ምርምር | እስከ 9% | |
| | | • አንድ ምርምር | እስከ 6% | |
| 3 | 8% | ለተማሪዎች የሚጠቅም የሳይንስና የሂሳብ የማስተማሪያ ማጣቀሻ/አጋዥ መጽሐፎችን ማዘጋጀት (የላብራቶሪ ማንዋሎች፣ ሞጅሎች ፣ወዘተ)<br>• ሶስትና ከዚያ በላይ አጋዥ | እስከ 8% | % |
| | | • ሁለት አጋዥ | እስከ 6% | |
| | | • አንድ አጋዥ | እስከ 4% | |
| 4 | 8% | ሽልማቱ በሚሰጥበት የትምህርት ዘመንና ከዚያ ቀደም ባለው ዓመት መምህሩ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር ተዛማጅ የሆነ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ በትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ወይም በሌላ ቦታ ማዘጋጀትና መጠቀም<br>• ዘጠኝና ከዛ በላይ | እስከ 8% | % |
| | | • ከ6 — 8 መርጃ መሳሪያዎች | እስከ 6% | |
| | | • ከ3 — 5 መርጃ መሳሪያዎች | እስከ 4% | |
| 5 | 6% | ንድፈ ሐሳብን ተግባራዊ ለማድረግ የቤተ ሙከራ አጠቃቀም<br>• ቤተ-ሙከራ ሁልጊዜ መጠቀም | እስከ 6% | % |
| | | • ቤተ-ሙከራ አልፎ አልፎ መጠቀም | እስከ 3% | |
| 6 | 6% | የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማቀላጠፍ እና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ብቃት ለማሻሻል ያለው ተነሳሽነት<br>• በትርፍ ጊዜ የማጠናከሪያ ክፍል ማመቻቸት | እስከ 3% | % |

---

[2] የተሰሩት ናሙናዎች ውስብስብነት፣ ብዛት እና ችግር ፈቺነት ከግምት ውስጥ ይገባል።

[3] የምርምር ስራዎች ችግር ፈቺነት እና ከሳይንስና ሒሳብ ትምህርቶች ጋር ያላቸው ተያያዥነት ከግምት ውስጥ ይገባሉ፤ የተሰሩት የጥናት ሰነዶች ኮፒ ለፌደራል ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ መላክ ይኖርባቸዋል

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • በጉድኝት ማዕከል የላቀ ተሳትፎ ያደረገ | እስከ 3% | % |
| | | | ድምር 6% | ድምር ____ % |
| 7 | 5% | ሳይንስን በማስተማርና በተግባር ለማሳየት ያለ ችሎታ፤ በሚስተምረው ትምህርት ያለው ዕውቀትና የማስተማር ዘዴ<br>• በትምህርት አይነቱ ያለው ዕውቀት | እስከ 2% | % |
| | | • የማስተማር ችሎታ | እስከ 2% | % |
| | | • የቋንቋ ክህሎት | እስከ 1% | % |
| | | | ድምር 5% | ድምር __ % |
| 8 | 5% | በትምህርት ቤቱ ከማስተማር በተጓዳኝ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ያለው ተሳትፎ<br>• በትምህርት ቤቱ የሳይንስ ክበብ ለመመስረት/ለማጠናከር ያደረገው አስተዋፅኦ | እስከ 3% | % |
| | | • በሳይንስ ክበብ የማስተባበር ሥራ | እስከ 1% | % |
| | | • በሳይንስ ክበብ ንቁ ተሳታፊ መሆን | እስከ 1% | % |
| | | | ድምር 5% | ድምር % |
| 9 | 5% | በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ ያለው/ያላት አርአያነትና የተማሪዎች አያያዝ<br>• እጅግ በጣም ጥሩ | እስከ 5% | % |
| | | • በጣም ጥሩ | እስከ 4% | |
| | | • ጥሩ | እስከ 3% | |
| | | | ከ100% ያገኘው ጠቅላላ ድምር ውጤት ___ % | |

አባሪ 2

## ምድብ II ፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሳይንስ መምህራንና ተማሪዎች የሽልማት መስፈርት

### ሀ. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | ክብደቱ ከ100% | መስፈርት | የሚሰጠው ነጥብ መጠን | በግምገማው ያገኘው ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 50% | የፈጠራ ሥራን በተግባር ማሳየትና ጠቀሜታው መግለጽ [4]<br>• የፈጠራ ሀሳብ በማመንጨት ወደ ንድፍ የለወጠና፣ ንድፍን በተግባር (ሞዴል፣ናሙና ወዘተ) በመስራት ያሳየ፣ | እስከ 50% | % |
| | | • ንድፍን በተግባር (ሞዴል፣ናሙና ወዘተ) በመስራት ያሳየ፣ | እስከ 47% | |
| | | • ሀሳብን በማመንጨት በተግባር (ሞዴል፣ናሙና ወዘተ) በመስራት ያሳየ፣ | እስከ 44% | |
| 2 | 15% | ሽልማቱ በሚሰጥበት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት በሳይንስና በሂሳብ ትምህርቶች ያስመዘገበው አማካኝ የፈተና ውጤት<br>• ከ95 — 100 ያለው | እስከ 15% | % |
| | | • ከ90 — 95 ያለው | እስከ 13% | |
| | | • ከ85 — 90 ያለው | እስከ 11% | |
| | | • ከ80 - 85 ያለው | እስከ 9% | |
| 3 | 15% | የተማሩትን ትምህርት በቤተ ሙከራ ማሳየትና በትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የተሰሩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ፣ሞዴሎች ቻርቶች ወዘተ.<br>• በቤተሙከራ የተሰሩ ስራዎች፣ | እስከ 8% | % |
| | | • በትምህርት ማዕከል የተሠሩ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አይነትና ብዛት፣ | እስከ 7% | % |
| | | | ድምር 11% | ድምር % |
| 4 | 6% | በት/ቤት ባሉ ተጓዳኝ ተግባራት ላይ መሳተፍ<br>• የተለያዩ ሳይንሳዊ ዕሑፎችንና አዳዲስ ግኝቶችን በትምህርት ቤቱ ሚዲያዎች ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ማሰራጨት፣ | እስከ 4% | % |
| | | • በሳይንስ ክበብ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ | እስከ 2% | % |
| | | | ድምር 10% | ድምር % |
| 5 | 9% | በማጠናከሪያ ትምህርቶችና በቡድን ጥናት ለመጠቀምና ክህሎትን ለሌሎች ለማካፈል ያለው ተነሳሽነት፣<br>• በማጠናከሪያ ትምህርት ላይ የተደረጉ ተሳትፎዎች፣ | እስከ 3% | % |
| | | • በቡድኑ ጥናት ላይ የታየ/የተደረገ ተሳትፎ | እስከ 3% | % |

[4] የተሰሩትናሙናዎችውስብስብነት፣ብዛትእናችግርፈቺነትከግምትውስጥይገባል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ክህሎትን ለሌሎች የማካፈል ተነሳሽነት | እስከ 3% | % |
| | | | ድምር 9% | ድምር % |
| 6 | 5% | የተማሪው ባሕሪና ዲሲፕሊን<br>• ሕግና ደንብን ከመጠበቅ አኳያ፣ | እስከ 3% | % |
| | | • ከደባል ሱስ የፀዳ ከመሆን አንፃር፣ | እስከ 2% | % |
| | | | ድምር 5% | ድምር % |
| | | | ከ100% ያገኘው ጠቅላላ ድምር ውጤት | % |

## ለ. የሁለተኛ ደረጃመምህራን የሽልማት መስፈርት

| ተ.ቁ | ክብደቱ ከ100% | መስፈርት | የሚሰጠው ነጥብ መጠን | በግምገማው ያገኘው ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 45% | በትምህርት ቤት ውስጥ የተሰሩ ችግር ፈች የፈጠራ ሥራ /ናሙናዎች [5]<br>• ሶስትና እና ከሶስት በላይ ናሙናዎች | እስከ 45% | % |
| | | • ሁለት ናሙናዎች | እስከ 40% | |
| | | • አንድ ናሙና | እስከ 35% | |
| 2 | 12% | ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር የተጣጣመና ተቀባይነት ያለው የተግባር ምርምር ሰርቶ ማቅረብ<br>• ሶስትና ከዚያ በላይ ምርምሮች | እስከ 12% | % |
| | | • ሁለት ምርምሮች | እስከ 9% | |
| | | • አንድ ምርምር | እስከ 6% | |
| 3 | 10% | ለተማሪዎች የሚጠቅም ደጋፊ/ማጣቀሻ የማስተማሪያ መጽሐፍቶችን ማዘጋጀት (የላቡራቶሪ ማንዋሎች ፣ሞጁሎች ወዘተ)<br>• ሶስትና ከዚያ በላይ ደጋፊ | እስከ 10% | % |
| | | • ሁለት ደጋፊ | እስከ 8% | |
| | | • አንድ ደጋፊ | እስከ 6% | |
| 4 | 10% | ሽልማቱ በሚሰጥበት የትምህርት ዘመንና ከዚያ በፊት ባለው ዓመት በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ለማስተማር የሚረዱ የመርጃ መሳሪያዎችን በትምህርት ማእከል ወይም በሌላ ቦታ ማዘጋጀት<br>• ዘጠኝና ከዚያ በላይ | እስከ 10% | % |
| | | • ከ 6 — 8 መርጃ መሳሪያዎች | እስከ 8% | |
| | | • ከ 3 — 5 መርጃ መሳሪያዎች | እስከ 6% | |

---

[5] የተሰሩት ናሙናዎች ውስብስብነት፣ ብዛት እና ችግር ፈቺነት ከግምት ውስጥ ይገባል። ምርምር ስራዎች ችግር ፈቺነት እና ከሳይንስና ሒሳብ ትምህርቶች ጋር ያላቸው ተያያዥነት ከግምት ውስጥ ይገባሉ፤

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 5 | 8% | ንድፈ ሐሳብን ተግባራዊ ለማድረግ የቤተ ሙከራ አጠቃቀም<br>• ቤተሙከራን ሁልጊዜ መጠቀም | እስከ 8% | % |
| | | • ቤተሙከራን አልፎ አልፎ መጠቀም | እስከ 6% | |
| 6 | 5% | ለትምህርት ዓይነቱ ያለው ዕውቀትና ሳይንስን በተግባር ለማሳየት ያለው የማስተማር ዘዴና ብቃት<br>• በትምህርት ዓይነቱ ያለው ዕውቀት | እስከ 2% | % |
| | | • የማስተማር ዘዴ ችሎታ | እስከ 2% | % |
| | | • የቋንቋ ክህሎት | እስከ 1% | % |
| | | | ድምር 5% | ድምር % |
| 7 | 5% | በትምህርት ቤቱ ከማስተማር በተጓዳኝ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ያለው ተሳትፎ<br>• በትምህርት ቤቱ የሳይንስ ክበብ ለመመስረት ለማጠናከር የተደረገ አስተዋፅኦ | እስከ 5% | % |
| | | • የሳይንስ ክበብን የማስተባበር ስራ | እስከ 3% | |
| | | • በሳይንስ ክበብ ንቁ ተሳታፊ መሆን | እስከ 2% | |
| 8 | 5% | በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ ያለው ባህሪ፣ አርአያነት<br>• እጅግ በጣም ጥሩ | እስከ 5% | % |
| | | • በጣም ጥሩ | እስከ 4% | |
| | | • ጥሩ | እስከ 3% | |

ከ100% ያገኘው ጠቅላላ ድምር ውጤት ______%